# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

# ትንበያ መጽሔት

## ከፌብርዋሪ 11-20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከፌብርዋሪ 21-28 እና ከማረች 1-10/2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 2025

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ............ - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ............ - 2 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ............ - 2 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ............ - 2 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ............ - 2 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ............ - 3 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ............ - 3 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ............ - 4 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ............ - 4 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-28, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ............ - 5 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-28, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ............ - 5 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ............ - 6 -

ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከማርች 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ............ - 6 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ............ - 7 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ............ - 7 -



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፈው አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምዕራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሸለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግበዋል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአይደር 39.1፣ በአልጌ 20 እና12፣ በአርጆ 22.4፣ በአፅቢ 46.2፣ በበደሌ 14.5፣ በቡሬ 13.6፣ በጭራ 22.7፣ በደብረ ብርሃን 20.7፣ በድምቢ ዶሎ 26፣ በዳንግላ 20.8፣ በጋቲራ 10.5፣ በጊምቢ 15.4፣ በካቺሴ 22.6፣ በላሊበላ 12.6፣ በላሬ 11፣ በማሻ 12.4፣ በንፋስ መወጪያ 11.7፣ በሻምቡ 10.8፣ ወግል ጤና 12.4፣ በወረኢሉ 15.7 እንዲሁም ባበቱ 11.1 ሚሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በሰሜን ምዕራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከ11-50 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 2 እና 3) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ የአማራ ከአማራ ክልል ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና የከፋ ዞኖች ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 4) ፡፡

በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ጋምቤላ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35.0-43.0 ዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል (ካርታ 1) ።




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 1  እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025

ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025

ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረዉ
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የፌብሪዋሪ የሁለተኛው አስር ቀናት በምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምስራቅ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ እርጥበት እንደነበራቸው የተሰበሰቡ የእርሻ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህም የተገኘው እርጥበት በተለይም የበልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግ እና አስቀድመው የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴ ለሚያካሂዱ አካባቢዎች ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የፌብርዋሪ ሁለተኛ አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የሀገራችን ተፋሰሶች ደረቃማ የአየር ሁኔታ ስር እንደቆዩ የተተነተኑ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም ግን አልፎ አልፎ ከነበረው የደመና ሽፋንና የዝናብ ሁኔታ ጋር ተያይዞ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ በላይኛውና በመካከለኛው አባይ፣ በላይኛው ኦሞ ጊቤና በባሮ አኮቦ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

እንዲሁም በጥቂት የአፋር ደናክል እና የተከዜ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ የገፀ ምድር የውኃ ሀብትን በመጠኑም ቢሆን የማሻሻልና ባለበት እንዲቆይ የማስቻል አቅም ነበረው (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በፌብሪዋሪ ሶስተኛው  ስምንት ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ መደበኛ ቦታዎቻቸውን የሚይዙበትና የሚጠናከሩበት ጊዜ በመሆኑ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋንና የእርጥበት መጨመር ይኖራል፡፡


በሚቀጥሉት ስምንት ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ገፅታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በሆኑት የመካከለኛዉ፣ የሰሜን ምስራቅ እና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ቄልም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን እና የመካከለኛዉ ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የምስራቅ እና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ፣ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በሌላ በኩል በጋምቤላ፤ በሰሜን ምዕራብ፤ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)።




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-28, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-28, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች የመጀመሪያው አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት አንፃራዊ መጠናከር እያሳዩ በመሄድ የወቅቱ ዝናብ በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋና እየተጠናከረ ይመጣል፡፡

በመጪዎቹ የማርች አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአንጻራዊ ሁኔታ እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 9)፡፡

Total Rainfall (mm) for 1-10 Mar 2025




ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከማርች 1-10, 2025

የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የፌብርዋሪ ስምንት ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ቀላል መጠን ያለው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ከበልግ ወቅት መጀመር ጋር ተያይዞ በዚህ ወቅት የሚገኘው እርጥበት የበልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ስለሚያሻሽል የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የበልግ ወቅት ሰብሎችን አስቀድሞ ለመዝራት የሚያስችል በመሆኑ አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ ዘር ለመዝራት የቅድመ ዝግጅት ስራ ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የፌብሩዋሪ ስምንት ቀናት አብዛኛዎቹ የሀገራችን ተፋሰሶች ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር እንደሚቆዩ የሚጠበቅ ቢሆንም፤ በላይኛውና በመካከለኛው አባይ፣ በላይኛውና በመካከለኛው አዋሽ፣ በላይኛው ኦሞጊቤና ባሮ አኮቦ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አዋሳኝ ተፋሰሶች መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታን ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ ወቅት ከመጀመሩ ጋር ተያይዞ በጥቂት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገራችን ተፋሰሶች ላይ የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት የገጸ ምድር የውሃ ሀብትን ባለበት እንዲቆይ ከማስቻል አንጻር የተወሰነ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et